***“ ፕሮፓጋንዳና ማስፈራራትን ወጣቱ ስለተለማመደው አይፈራውም እንዲያውም ምሬቱ እየጋለ ይበልጥ ለነጻነት ይበልጥ ለትግል ይነሳሳል እንጂ “ ወጣት አርአያ።***




ዛሬ የካቲት 20 ቀን 2001 የAንድነት ፓርቲ ሊቀ መንበር ወሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ በሕገወጥ መንገድ ተይዘው ቃሊቲ ከታሰሩ ልክ ሁለተኛ ወራቸው ነው፡፡ባለፈው ወር በፓርቲው ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እንደተካሄደው ሁሉ ዛሬም ተከበረ፡፡

በዛሬው እለትም እንዳለፈው ሁሉ የቃሌ የሻማ ምሽት ዝግጅት በሃላፊነት ወስደው ያዘጋጁትና በዕለቱ ተናጋሪዎችን ገጣሚያንን የጋበዙትም እነሱው ወጣቶቹ ነበሩ፡፡አዲሱ የፓርቲው ጽ/ቤት ለዝግጅቱ ከቀድሞው ግቢ በበለጠ መልኩ ሰፊና አመቺ ስለነበር የቦታ ጥበት አላጋጠመም፡፡
በቃሌ ምሽት ላይ ወ/ሮ አልማዝ የብሩኬ እናትና ሃሌ ውድ ልጇ በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ተጋብዘው ስለነበር በሰዓቱ ነበር የመጡት፡፡ሃሌ ገና በግቢው ገብታ ባካባቢው ያሉት ሰዎች መሃል የምታውቃቸውን ስታይ መፈንጠዝና መቦረቅ የጀመረጭው ከመኪና ሳትወጣ ነበር፡፡በግቢው የነበሩት በሙሉ ወ/ሮ አልማዝንና ሃሌን በክብርና በፍቅር ከተቀበሏቸው በኋላ ሌሎቹ እስኪመጡ ማረፊያ ተደርጎላቸው ሁሉም ባሉበት እየሄደ ከበሬታ የተሞላበትን ሰላምታ እየሰጡና አብረውም ፎቶግራፍ ሲነሱ ቆዩ፡፡

የጥሪው ሰዓት 11 ተኩል ሲደርስ የፕሮግራሙ አዘጋጆች ታዳሚውን ወደ ተዘጋጀው ቦታ እንዱሄድ በመጋበዝ ቦታ ካስያዙ በኋላ የዕለቱ ፕሮግራም መሪ ታምራት ታረቀኝ የምክር

ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል፤የወጣት ኮሚቴ ሰብሳቢ እንግዶቹንና የበዓሉን አዘጋጆች ካመሰገነ በኋላ የዝግጅቱን ኮሚቴ ወክሎ ወጣት አርአያ ንግግር እንዲያደርግ ጋበዘ ወጣት አርአያም እንግዶቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ካለ በኋ ለጥቆ በዓሉን በመስመልከት «ወጣቱ ከብርቱካን ታማኝነትን፤ጥንካሬን አደራ ጠባቂነትን ተምሯል፡፡ወጣቱ የራሱን ጉዳይ እራሱ መወሰን እንዳለበትና በራሱ ሕሊና መመራት እንዳለበት ተምሯል፡፡ገዢው መንግሥት መሪያችንን ብርቱካንን ሲያስር መልዕክቱ ግልጽ ነው፡፡ እኛን ወጣቶችን አርፋችሁ ተቀመጡ ነው ያለን እኛ ደሞ አርፈን የምንቀመጠው መሪያችን ብርቱካን ተፈታ የዴሞክራሲ ተግባራዊነት ሲረጋገጥ፤ፍትሃዊነት ሲሟላ ሰብዓዊ መብት ሲከበር መሆኑን እንዲያውቅልን እንፈልጋለን፡፡

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወጣቱን ሰብስበው በጥቃቅን ብድርና ሥራ ላይ እንዲያተኩርና እዳው ለመክፈል በማሰብ ወጣቱን ወደ ፖለቲካ እንዳይመልስ ለማድረግ ቢሞክሩም ወጣቱ አውቋልና ገብቶታልና ሲያወሩ ሰማ እንጂ አላዳመጣቸውም፡፡ ወጣቱ አሁን የሚያዳምጠው ሃገሩን ነው፡፡ ብርቱካንን ነው፡፡ አንድነትን ነው፡፡ ነጻነትን ነው፡፡ አጉል ፕሮፓጋንዳና ማስፈራራትን ስለተለማመደው አይፈራውም እንዲያውም ምሬቱ እየጋለ ይበልጥ ለነጻነት ይበልጥ ለትግል ይነሳሳል እንጂ፡፡» በማለት ስሜት የሚቀሰቅስ ንግግር አድርጓል፡፡

በቀጥሎ ወደ መድረክ የተጋበዘው ወጣት ገጣሚ ስለሺ ሃጎስ ነበር፡፡ ስለሺ ባለፈው ዝግጅት አብርሃም ልጁን ለመስዋዕት ለማቅረብ ሶስት ቀን እንደተሰጠው ላንቺም ብሎ የገጠመው ወጣት ነው ወጣት ስለሺ ሃጎስ ያቀረበው ግጥም የሰዉን ስሜቱን የፈነቀለ ነበር፡፡

ስምሽ ጠፍቶ ዙርያ ገባሽ
በላይ ያልሽን በታች ሆነሽ

መኖርሽ ቢያሳስበኝ
ልመናሽ ቢያሳፍረኝ

ከመቃብር ሆኜ አለቀስኩ ኢትዮጵያዬ
ስቅስቅ.....ስቅስቅስቅ...ብዬ

ወንድ አይብቀልብሽ ብዬ እርግማኔን ባጸናም
እግዜር እንደሁ ይወድሻል መቼም ባንቺ  አይጨክንም

የእኔንም እርግማን ሳይተው አንቺንም መና እንዳይተውሽ
ወንድ ቢጠፋም ቅሉ የሴት ጀግና ፈጠረብሽ
እናም ዛሬ ከመቃብሬ የምስራቹን ይሄውልሽ
እርግማኔ አንስቻለሁ ሀሴት አርጊ ደስ ይበልሽ

የበላይ ጸጸት

ተሳስቼ ነበር አብጄ እናቴ
ወንድ አይብቀልብሽ ማለቴ

ያሉላ የካሣ
የባልቻ ያብዲሳ

ዛራቸው ሰፍሮብኝ
እምቢ  ሃገሬን አትንኩ ባልኩኝ

በነማይ  በጎንቻ ጫካ ባባይ በረሃ ዋሻ ኑሬ
ከምኞት ጋር ተቃቅሬ

በክብርሽ በደማሁኝ
ላንድነትሽ ዘብ በቆምኩኝ

ብድራቴን ሞት ሲያደርጉ ሲሸልሙኝ
ስቅላቴን ነበር እኮ ወንድ አይብቀልብሽ ማለቴ

ወንድ ጠፍቶ ባገር ምድርሽ
ከቸችግር አዝመራ ረሃብ እያጨድሽ
መከራ አበራይቶ ሰቆቃ እየወቃሽ

መከፋትሽ የሚከፋውን ረሃብሽ የሚርበው ቆራጥ ጀግና ይብቀልብሽ
ቅን አስተዋይ ትሁት መሪ ይንገስብሽ
ሰው ሲጠፋ ሰው አትጪ ሃገሬ ሰው ይብቀልብሽ

ወንድ ከግንባሩ ደም እንጂ ካይኑ እምባ አይወርድም ብትይኚም
ዛሬ አለቀስኩ  ኢትዮጵያዬ እንደድሮው አቅም የለኝም

ግና የፈሪ እንጀት ይዞ ነው አትበይኝ  አንጀቴስ የቆራጥ ነበር
መድፍን በጋሻ የሚመክት ከመርዝ ጋር የሚታገል ባነድራሽን አቅፎ ሚሞት አንጀቴስ የቆራጥ ነበር
.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..
ከመቃብር ተዘርግቼ  እጣ ፈንታሽን ሳየው
ህልውናሽ ያሳስበኛል እንዴት አርጌ ልቻለው

ባድመሽን ሽራሮሽን ቀይ ባሕርን አስረከበሽ
ጆሮ ዳባ ልበስ ስትይ ስትጨፍሪ ይባስብሽ
አልሰጋሁም ለመተማ አልሰጋሁም ለሞያሌ ለተቀሩት ጠረፎችሽ
ደግነትሽ ሲበዛብኝ ፈራሁ አንጂ ላዲስአባሽ



ወጣት ስለሺ ግጥሙን ካቀረበ በኋላ ተከታዩ ተረኛ ባለፈው የወጣቶች የግጥም ምሽት ላይ ምርጫ ጥሩ ነበር ተቃዋሚ ባይኖር ያለው ወጣት ገጣሚ ሰሎሞን ሞገስ ቃሌ ብሎ

ከማውቀው ከማመነው በቀር ሌላ የምለው ባይኖርም
እምነት እውነቴን ቀብሬ መርዶ ላይ አልቀመጥም

አልችልም፤ አልችልም እኔ
እብለትን ለማመቻቸት ሽተትን መያዝ ከጎኔ

አልችልም አልችልም ከቶ
በገዛ አገር ላይ መቀመጥ አንገትና ልብን ደፍቶ

እናም ይሄው ቃሌ ካሻ
ከወህኒ ጉረኖ መለስ ምናልባት በመጨረሻ

እናንተ ያስገረማችሁ ያፌዛችሁበት እውነት

ማተብ መስቀሌ መሆኑን ብታውቁ ምን ነበረበት;
ለሃቅና ለእውነት ፍቅር
ለህግና ፍትሕ ክብር

ለሱ-ኮ ነው ምኖረው
ለሱኮ ነው የምቆመው

የምሰደብ የምመታ
የምታሰር የምፈታ

ሕግ እኮ ነው ቁም ነገሬ
ለሱ ኮ ነው ድካም ትግሌ
ሕገ ወጥን  አሜን ብዬ ማስመሰልን አልፈቅደውም
መቼም መቼም አልችለውም
አልችለውም አለምደውም

ነጋሪት እየጎሰሙ ቀን ቆጥረው እያስፈራሩኝ
ሶስት ቀን ሰጠንሽ አሉኝ
ሁለት ቀን ይቀራል አሉኝ
አንድ ቀን ነው ያለሽ አሉኝ
ግማሽ ቀን ቀርቶሻል አሉኝ

ይሔው ጀምበር ዘቅዝቆ ጨለማ ሊውጠኝ ሲሻ
ከወህኒ ጉረኖ መለስ ምናልባት በመጨረሻ

መቼምአይለወጥ ቃሌ
መጪው ትውልድ ይፍረድብኝ ምስክር ትሁነኝ ሃሌ

ከዚህ ሌላ ምን እላለሁ
የጎልጎታዬን ዳገት በፍቅር  እወጣዋለሁ
የሠላም የትግል ሜዳን በአጋም እሾህ እያጠራሁ
የሕግ አግባብ ገደል ገብቶ ጉልበተኛ ካሳመረው
ለዚህ ቀልድስ ለዚህ ተረት
እኔ አልችልም እሺ ማለት
እብሪት ሸፍጥን ላዝለው ላቅፈው
ከቶ አልችልም እሺ ልለው
እኔ አልችልም አሜን ልለው፡፡



የሚለውን ግጥሙን አስደመጠ፡፡
ከግጥም ሌላ የቀረበው ብርቱካን እንደ ሰው  እንደፖለቲከኛ የሚለው ጽሑፍ ነበር፡፡
አቅራቢውም አቶ ደበበ እንዲህ አለ፡-



**ብርቱ እንደሰው ብርቱ እንደፖለቲከኛ ባጭሩ ብርቱ-ካሕን**

በባህላችን ሰውን በሕይወት እያለ በጠንካራ ጎኑ ማመስገን በደካማ ጎኑ የመውቀስ ባሕል የለንም፡፡ ግልጽ ለመሆን ብቃት ያላቸው ቢኖሩም አብዛኛዎቻችን ግን የጎንዮሽ አካሄድን የምንመርጥ ነን፡፡ ፊት ለፊት ለባለጉዳዩ ከመናገር ይልቅ ከጀርባው ስለሱ ባሕርይ ማውራትን እንመርጣለን ለምን ግልጽነት የለንምና፡፡

በተለምዶ አንድ ሰው ስለሌላ ሰው ማውራት ሲጀምር እሱ እኮ ብሎ ከጀመረ ችግር አለበት ብዬ አስባለሁ እኮን ትቶ እሷ ወይም እሱ ብሎ የሚጀምር ጥቂት በመሆኑ፡፡ እኮ ዛቻም ነው እኮ አፍራሽም ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ነደሞ ደግ ጎንም አለው እንዳጠቃቀማችን፡፡
እምነት የሌለው ሰው ቀናነት ይጎለዋል፡፡ የማያምን ሰብዓዊነቱ ምልአት አይኖረውም፡፡ፈሪሃ ፈጣሪ ሳይኖረን ስለ ሰው ደህና ማሰብ ለሰው ደህና መመኘት ሊቻለን አይችልም፡፡ ከምንም በላይ ብርቱ ካህን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላት ናት፡፡ ስለዚህም ሰብዓዊ ናት፡፡

ዛሬ መሪያችን ብርቱ ካህን ከታሰረች ሁለት ወር ሆናት፡፡ ሁለት ወር ብቻዋን፤ሁለት ወር በጠባብ ምቾት በሌለው ቦታ፤ ሁለት ወር ከቤተሰብ ተለይታ፤ሁለት ወር ብቻዋን እያወራች፤ሁለት ወር በአሳሪዎቿ ግልምጫና ዛቻ መከራዋን እያየች፡ ሁለት ወር ከምትወዳት ልጇ ከሃሌ ተለይታ፡፡
እኛ ደሞ እዚህ ነን፡፡ ከቤተሰባችን ጋር፤ በሞቀ ቤታችን፤ባሰኘን ሰዓት የፈለግነውን እያደረግን፤ ከምኝታ ቤት ምግብ ቤት ከምግብ ቤት ሳሎን እያልን፡፡ ያም ባይኖረን ከቤት ወደጸሃይ ሲበቃን ወደቤት ጥላ ውስጥ እንደፈለግነው እየተመላለስን፡፡ ግልምጫ የለ፤ዛቻ ሳይደርስብን፡፡

## ወድ ወገኖቼ

ብርቱ ካህንን ሳውቃት ጥቂት ዓመታት አልፈውኛል፡፡ ከምርጫ 97 በፊት ነው እውቂያችንና በመጠኑም ቢሆን ለምስክርነት እንብቃቃለን ብዬ አምናለሁ፡፡
ብርቱ ካህን እንደሰው ሩህሩህ፤ አሳቢ፤ሃላፊነት የሚሰማት፤የተቸገረን የምትረዳ፤ቀና ሰው ናት፡፡ልጅ አላት የምትወዳት፤ብቻ እንደሌሎቻችን የልጇን ልደት አብራ ለማክበር አልታደለችም፡፡ በአራት ዓመት ዕድሜ ልጇ ጋር ልደት ያከበረችው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ሰው ነችና ይህ ይጎዳታል፡ ትታመማለች፡፡«እንግዲህ ጨዳራዬ ሊነሳብኝ ነው የጠቆረ ፊት አየሁ» የምትለው አባባል አላት፡፡

ማንም ሰው እንደሚጎዳው ብርቱ ካህንም ሰው ነችና ትጎዳለች፡፡ጉዳቷን ግን ውስጧ ነው የምትይዘው፡፡ተጎዳሁ ብላ ቂም በቀል ግን አታውቅበትም፡፡ ይልቅስ ሲበድሏት ሰበቡን ለማወቅ ነው ጥረቷ፡፡ ሰው በመሆኗ ሲከፋት ያስታውቅባታል፡፡መከፋቷን ደብቃ ላይ ላዩን መሳቅን ብዙም ስለማታውቅበት አኩራፊ መስላ ልትታይ ትችላለች፡፡ አኩራፊም አይደለች ስታኮርፍም ስለማታውቅበት አታምርም፡፡ ብርቱ ካህን ለቤተሰቧ ያለችው ብቸኛ ረዳት ናት፡፡ብቸኛ እናቷ ካለሷ መቀመጥ ሰልችቷቸዋልና «እኔ ለልጅ ናፍቆት የታደልኩ ነኝ» ይላሉ፡፡ ብርቱ ካህን ደግሞ እንደማንኛውም ሰው ችግርና መከራን መቅመስ ልዩ አያደርገኝም ብላ የምታምን ዝም ብዬ ጥሩ ሰው ናት ብላት ይሻለኛል፡፡

## እንደፖለቲከኛ ደግሞ

ቆራጥ ነች፡፡የዓላማ ጽናት አላት፡፡የሕዝብ አደራ ይከብዳታልና ተሸክማ መውደቅ ቀርቶ መንገዳገድ እንኳዋን አትፈልግም፡፡ ፖለቲካ መጠፋፊያ ሳይሆን ቂም በቀል መወጣጫ

ሳይሆን መማማርያ ደግ ማሰቢያ የህዝብን ችግርና ሰቆቃ ማጥፊያ ሰብዓዊ ክብርን ማስጠበቂያ፤ ነው ብላ ታምናለች ተግባራዊ የምታደርገውም ያንን ብቻ ነው፡፡

ለራሷ መከበር ብላ የምታደርገው አንዳችም ጉዳይ የለም፡፡ፖለቲካን እንደ ነጻ ማውጫ መሳርያ፤የልማት አውታር ማስመርያ፤የዕድገት በር መክፈቻ ነው ብላ ነው የምታስበውና የምትሄደውም ያንን ይዛ ነው፡፡ አሁንም ስትታሰር ያንን ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡የተጠየቀችውን በሁለት መስመር ሰጥታ ተመሳስላ ከእስር ለመዳን ስትችል እሷ ግን እውነትን ይዛ የሂደቱን ዝርዝር ከሕግ ጋር በማጣቀስ እውነቱን ከተበች፡፡ የሕዝብን አደራ ቃሌን አጥፌ አላጠፋም ብላ ነው ለዳግም እስር የተዳረገችው፡፡ብርቱ ካህን መሪያችን ነበረች ነች ወደፊትም እሷው ነች የምትመራን ብለን ቃል ገብተናልና ያንን ቃል ከማፍረስ ያንን ቃል ከመጣስ የበለጠ የፖለቲካ ከሳራ አይኖርምና ጥንካሬ ይስጠን፡፡

አንድ ጊዜ ብርቱ ካህንን ከቶሮንቶ ወደ ቫንኩቨር ስንበር ስለ አቶ ስዬ አብርሃ የዋስ መብት አሰጣጧ ጉዳይ አነሳሁባት፡፡ «ብርቱ እንዲያው ሁል ጊዜ በሃሳቤ ያለ አንድ ነገር ላንሳብሽ፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው አቶ ስዬ አብርሃ ኤርትራ እንድትገነጠል ያደረጉ፤የብሄር ፖለቲካ ልክ ነው ብለው የሚያምኑ፤የባንክን የዓየር መንገድን ሠራተኞች በቦርድ ሊቀመንበርነት የበተኑና ለረሃብና ለቸነፈር የዳረጉ ሰው ሆነው አንቺ ፊት ለፍርድ ሲቀርቡ እንዴት ብለሽ ነው የዋስ መብት ያውም በስንት ዳኞች የተከለከለውን የፈቀድሽው;» አልኳት

ሁላችንም እንደምናውቃት ብርቱ በመጀመርያ ሳቀችና «ብዙ ሰው ይህን እንደሚያስብና ግን አውጥቶ የጠየቀኝ እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ አንተ ግን ዛሬ አነሳሃው፡፡ አየህ እኔ በመጀመርያ ሕግን ተምሬያለሁ፡፡ ስማረው ደሞ ስርዓቱን ላከብር ለሕግ የበላይነት ልገዛ፡ ግራ ቀኝ አይቼ መዝኜ ፍትሕ ልሰጥ ነው፡፡ ከትምሕርት በኋላ ደሞ ወደ ሥራው ዓለም ስገባ ቃለ መሃላ ፈጽሜ ፍትህን ላልጎዳና በፍትሕ ስም ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር መብቱን ላልሸረሽር ቃል ገብቻለሁ፡፡ፍትሕ የራሱ የሆነ መመርያና ደንብ ያለው ሙያ ነው፡፡ፍትሕ እንዳይጣስ በወንበሩ ላይ መቀመጥ ማለት ቂም በቀል መወጫ ለማድረግ ሳይሆን ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡ በእኩል ደረጃ፡፡

ያን እለት አቶ ስዬ እኔ ችሎት ሲቀርቡ፤ለኔ የቀረቡት፤አቶ ስዬ አይደሉም አንድ ግለሰብ ፍጡር ናቸው፡፡እነህ ሰብዓዊ ፍጡር ደሞ ፍትሕ ሊሹ ነው የቀረቡት፡፡ አቃቤ ሕግ አጥፍተዋል ብሏቸዋል፤ያጠፉት ጥፋት በኔ ሕሊና መታየት ያለበት ጥፋተኛውና ያን ያልከውን ያደረጉት ስዬ አብርሃ ተብለው ሳይሆን አንድ ሰው ተብለው ነውና እኛ እኔ ችሎት የቀረቡት ሰው የተጠቀሰባቸው አንቀጽ የዋስ መብት ይከለክላል አይከለክልም ከደንቡና ስርዓቱ ጋር ነው አይደለም ብዬ ነው መጻሐፉን አገላብጬ ያየሁት፡፡ቁልጭ ብሎ የሰፈረው የዋስ መብት ይፈቅዳል፡፡ ስለዚህ ፈቀድኩ፡፡ተግባባን፡፡

እርግጥ የተቀመጥኩት ዳኝነት ባይሆንና ተመልካች ብሆንስ ኖሮ ያ ሌላ ነው፡፡ዳኝነትን ግን ለቂም በቀል መወጫ ለራስ ፍላጎት ማሟያ ለማድረግ የሚያስችለኝ ትምህርት መምህራኖቼ አላስተማሩኝም»ነበር ያለችኝ፡፡ እሷ እላገኘቸውም እንጂ ሕግ በሚዛን ከልኩ ሳይበልጥ ሳይጎድል ሰርታበታለች፡፡ዴሞክራሲያዊ ፍትሕን አሳይታናለች፡፡
ብርቱ ካህን የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓርቲ ሊቀመንበር ነች፡፡ ታስራም ሊቀመንበራችን ስትፈታም ሊቀመንበራችን ከዚህ ሌላ አማራጭ የለንም፡፡
ብርቱ ካሕን ወደ ቃሊቲ ስትወሰድ አደራ ብላን አደራ ጥላልን ነው የሄደችው፡፡«እኔ ብታሰርም እናንተ አንድ ሆናችሁ አንድነትን ጠብቃችሁ ለሕዝብ ልዕልና ቆማችሁ አብረን በያለንበት የሕዝብን አደራ ለመወጣት እንድንችል ጋሻ መከታ እንጂ ጉጠትና አሜኬላ ከመሆን ፈጣሪ እንዲጠብቃችሁ እጸልያለሁ እናንተም ለኔ ብርታት ጸልዩ ፈጣሪያችን ኢትዮጵያንና ሕዝቡን ይጠብቅ፡፡ ብላናለችና ቃሏን እንጠብቅ፡፡

አንድነት ፓርቲ የቅንጅት ወራሽ ነው ስንል መልካሙን ይዘን ጥንካሬውን ወርሰን ለመጓዝ እንጂ ስህተቶችንም ለመድገም እንዳይደለ ደጋግማ ስትለው የነበረ ራዕይዋ ነበርና ያንንም እናከብርላታለን፡፡ ለዚህም ነው ከሊቀመንበራችን ጋር አብረን እንዘልቃለን ብለን ቃል የገባነው፡፡

የአንድነትን አመራርና የአባላቱን ቆራጥነት የሚፈሩና የሚቀኑበት በተቻላቸው ሁሉ ለማዳከምና ጠንካራ ተፎካካሪ ሳይሆን ለንቋሳ ተቃዋሚ እንድንሆን ቢሞኙ ያ እንደነጎድጓድ የሚያስተጋባው የአባላት ፍቅርና እንደሱናሚ በመስቀል አደባባይ የተጥለቀለቀው ሕዝባዊ ሰልፍ መንፈሱ እንዳለ በመሆኑ ያንን የመጠበቅና ቃል የማክበር ሃላፊነት በእያንዳንዳችን ላይ የተጫነ የአንድነት አደራ ነው፡፡ አሁን ብርቱ ካህን የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ብቻ አይደለችም፡፡ አሁንማ ብርቱ ካህን የማትገፋ የማትደፈር የብረት መዝጊያችን ጠበቃችን ጠባቂያችን መከታችን ሆና ድምጻችንን በሷ ስም ላይ ከፍ አርጋ እያስተጋባች ነውና ከመቼውም የላቀ ከበሬታ ፍቅርና የዓላማ ጽናታችንን ልናረጋግጥላት ይገባል፡፡ ዓለም ሁሉ ብርቱ ካሕንን ዛሬ እያነሳት ስለሷ እየተሟገተ ነውና እኛም ከዚያ የተለየ በማድረግ የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ፈጣሪ ይጠብቀን፡፡ ለምንለው ታማኝ፤ ለፓርቲያችን ፅኑ፤ለመሪያችን መከታ፤ለሃገርና ለሕዝብ አለኝታነታችንን ለማረጋገጥ  ለራሳችንም ለሃገራችንም የማይታጠፍ ቃል እንግባ፡፡

<u>መድረሻ ያጡ ለት</u>

(ፍትሕን ላጣመሙ ታሕሳስ 2001)

ቀለም ነጠብጣቡ ብእር ብእርእሩ

ፊደል ውርግርጉ ቃላት ጥምብርብሩ

ምን እጆች ቢሾሉ ለፍርድ ጉዳ ጉዱ

የትግሉን በበልባል አይችሉም ሊጎዱ

ዳኛው ውትፍትፉ ክሱ ግሳንግሱ

ወደፊት ሲጠና ወጥቶ ጥምብ እርኩሱ

መቆሚያው የት ይሆን ስትወጠር ነፍሱ?

ዕውነት ስትሞግተው ሃቅ ሲወጥረው

ፍትሕ ካድከኝ ብሎ ጉሮሮውን ሲያንቀው

ውሳኔ አለወወጣም ሲል ላንቃውን ሲዘጋው

ክህደት ወጥሮ ለሃቅ ሲሞግተው

አዬ ጉድ ያን ጊዜ እዬዬ ያን ዕለት

ክብር እምክቡራን መድረሻ ያጡ ለት።

አመሰግናለሁ፡፡__